# ኢሕአፓ - ወክንድ

(የአደራ ቃል ግጥም ከአብርሃም በየነ፣ ሃምሌ 2001)

አዲሱ ካለፈው - ሂደት የቀጠለ፣
ታሪክ ሰንሰለት ነውና - የተቀጣጠለ፣
የቀደማዩን ውጥን - ኋለኛው የሚረከበው በውርስ፣
ትናንት የዛሬ ወላጅ ሲሆን - ነገም እንዲሁ የዛሬው ፅንስ፣
መሆኑን ልብ በልና - ኢሕአፓ - ወክንድ፣
አርማውን ስትረከብ - የዚያን ብርቅዬ ትውልድ፣
ለታሪክ ዕዳ የከፈለውን - የህይዎት ዋጋ፣
ያፈሰሰውን ደም - የቆረሰውን ስጋ፣
ለእኩልነት ለፍትህ ለአንድነት ሲል - ያየውን መስቅ፣
ህያው ታደርገው እንዲቻልህ - የዕምነት ማተቡን አጥልቅ።

የሰው ልጅ ስብዕናውን - በሆድ አምልኮ ለውጦ፣
ሰው ሰው መሆኑን ሽሮ - ህሊናውን ሸቅጦ፣
ለሆዱ ባደረበት አገር - ሰው ሆኖ መገኘት፣
ለዛሬው ዘመን ሰው - ብሂለ ዕምነት፣
መለኪያ መስፈርቱ - ብልጠትና ውሸት፣
በሆነበት ባህል - የዕውነት ዕውነትነት፣
ተክቸልችሎ የፋራ ፖለቲካ ነው - ሲባል ፀናት፣
በዚህ ዘማዊ የፖለቲካ - ስነ ልቦና፣
ባህል ውስጥ የተወለድክ - አካል ነህና፣
በእምነትህ ለመወገር - በራዕይህም ፈተና፣
የሚጠብቁህን እንቅፋቶች - አጢንና፣
ለዕምነቱ ፅናት - ዕዳ ከፋይ፣
ኢሕአፓ ብቻ መሆኑን - ሁሉም እንዲያይ፣
ታሪክን ዋቤ ጠርተህ - ምስክር፣
ሃቁን አስጎንጨው - በዘገር።

የትናንቷ ኢትዮጵያ - አፈሯ በደም ዕርሶ፣
ጎዳናዋ  በወጣት አፅም - ተልከስክሶ፣
በምትኩ ባድማዋ ባበቀለው  - አራሙቻ፣
በዘር በዘውጌ - በጎጥ በቋንቋ ጥላቻ፣
የማንነቷ ትውፊት - ከመሃል እስከ ዳርቻ፣
በፍርሃት ቆፈን - በስሌት ወኔው ተሰልቦ፣
ርሃብና እርዛት - ያለበሱትን ውርደት ተከናንቦ፣
በመኖርና ባለመኖር መሃል - በጣረሞት እስትንፋስ፣
የተስፋ ብርሃን ጮራ - በሩቅ እርቀት አድማስ፣
የህልም ያክል - ዕይታው ገፁ ደብዝዞ፣
በደመነፍስ ዕርምጃው - የሚራመደውን ጉዞ፣
በፈሰሰው መቅኑ - አቅሙ ኮስምኖ ናውዞ፣
ሸብረክ ባለበት ዘመን - የተፈጠርክ አካል ነህና፣
የነገውን መፃኢ ዕጣ - ወሳኙን የምስራች ፋና፣
ብስራቱን ነጋሪ - መልዕክተኛው ሆነህ እርግቡ፣
የዕምነትህ ቃል  - ፅናትህ እንዲሆነው ማተቡ፣
የማይበጠስ መሆኑን አረጋግጥለት -የቃልህ ገመድ ሸርቡ!!!!!